# በኦታዋ የግንቦት 20 በዓል በደማቅ ሁኔታ ተከበረ

የደርግ ስርዓት የተገረሰሰበትን 19ኛውን የግንቦት ሀያ በዓል ቅዳሜ ሰኔ 5 ቀን 2002 ዓ.ም በካናዳ ኦታዋ በርካታ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በተገኙበት በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል፡፡ በዚሁ ወቅት ጨቋኙን ስርዓት ለመገርሰስ ህይወታቸውን ለሰዉ ሰማዕታት የአንድ ደቂቃ የህሊና ፀሎት ተደርጓል፡፡

ተ/ጉ/ፈፃሚ ወ/ሮ አልማዝ አምሃ በዓሉን በንግግር ሲከፍቱ ከ19 ዓመታት በፊት ግንቦት ሀያ 1983 ዓ.ም በኢትዮጵያ ታሪክ ተወዳዳሪ የማይገኝለት የጨለማና የስቃይ ዘመን ተወግዶ አዲስ ምዕራፍ የተከፈተበት መሆኑ፣ በዚህም ህዝቦች እራስን በራስ የማስተዳደር፣ ባህላቸውንና ቋንቋቸውን የማሳደግ መብታቸው በፌዴራላዊ ስርዓት ተረጋግጧል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም የህዝቦች ኑሮ ለማሻሻል፣ የትምህርት፣ የጤናና ሌሎች መሰረታዊ አገልግሎቶችን ለማዳረስ፣ መሠረተ ልማቶችን ለማስፋፋት ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በተደረገው እንቅስቃሴ ጎልተው የሚታዩ እርምጃዎች ተወስደዋል ብለዋል፡፡ አያይዘውም ላለፉት ስድስት ዓመታት መንግስት የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ቀርጾ ባደረገው ርብርብ ኢኮኖሚያችን በተከታታይ 11% በላይ ያደገ ሲሆን ይህ ዕድገት ለሚቀጥሉት አስርተ ዓመታት እንዲቀጥል በማድረግ አገራችን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ መንግስትና ህዝብ የጋራ ራዕይ አስቀምጠው ጉዞውን ተያይዘውታል ብለዋል፡፡

በመቀጠልም የዘንድሮውን የግንቦት ሀያ በዓል የምናከብረው ዴሞክራሲያዊ፣ ፍትሃዊና ሰላማዊ የሆነው 4ኛው ብሄራዊ ምርጫ በተካሄደበት ማግስት መሆኑ የተለየ ያደርገዋል ብለዋል፡፡

ተ/ጉ/ፈፃሚዋ አክለውም 4ኛው አገራዊ ምርጫ ሰላማዊ፣ ፍትሃዊ፣ ዴሞክራሲያዊና በህዝብ ዘንድ ተኣማኒ እንዲሆን መንግስት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ከመነሻው ጀምሮ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነ-ምግባር ህግ እንዲቀረፅና በፓርቲዎች መካከል ውይይት የተካሄደበት ህግ ሆኖ እንዲወጣ መደረጉን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ፕሮግራማቸውን የሚያስተዋውቁበት የአየር ሰዓት አጠቃቀም ፍትሃዊ የነበረ መሆኑን ገልፀው ህዝቡም ከቀረበለት አማራጭ መካከል በሰከነና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ይወክለኛል ላለው ፓርቲ ድምፁን ሰጥቶ ምርጫው በሰላም ተጠናቋል ብለዋል፡፡

በመጨረሻም የአገራችንን ሁኔታ በንቃት በመከታተልና በጎውን በመመኘት ሲንቀሳቀሱ ለነበሩና ምርጫው በሰላም መጠናቀቁን በተናጠልም ሆነ በቡድን ለገለፁ የኮሚኒቲ አባላት በሙሉ ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

በዓሉን ያዘጋጀው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ኤምባሲ ሲሆን በበዓሉ ላይ ወደ 200 የሚጠጉ በኦታዋ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ተገኝተዋል፡፡ በዚሁ ወቅት በበዓሉ ላይ የተገኙ አንድ አንድ ግለሰቦች በዓሉ የሁሉም ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የታደሙበት መሆኑ ያስደሰታቸው መሆኑን ገልፀውልናል፡፡ በዓሉ መልዕክት አዘልና አዝናኝ በሆነ መልኩ ተከብሮ ውሏል፡፡